## የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)

## Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

ነሐሴ 16 ቀን 2003 ዓ.ም

### ጥሪ ለሀገር ወዳድ ዜጎች ሁሉ

### የአንድነት ኃይሎች መተባበር አስፈላጊና ወሳኝ ነው

የኢትዮጵያ ህልውናና አንድነት ላይ ለዘመናት ጥቃት ተሰንዝሮ በሕዝቧ ቆራጥ ተጋድሎ ሁሉም የወረራ ሙከራዎች-- ግብጽ፤ ቱርክ፤ ደርቡሽ፤ ጣሊያን፤ እንግሊዝ-- አፍረው ወደ መጡበት ተመልሰዋል። የእጅ አዙር ቅኝ ገዢዎች--አሜሪካና ሶቭየት ህብረት--ጸረ ሕዝብ አገዛዞችን በቅጥረኛነት ይዘው የሀገራችንን ሉዓላዊነት ቢዳፈሩም የሕዝባችን ታሪክ በዓለም አቀፍ ደረጃ ጀግንነትና ቆራጥነት ያንጸባረቀ አኩሪ ታሪክ መሆኑ የሚካድ ኣይደለም። ሀገራችን ኢትዮጵያ የነጻነትና የኩራት አርዓያ ሆና የቆየች ናት። የቅርብና የሩቅ ጠላቶችንም ያሳፈረች ኩሩ ሀገር ናት።

ሀገርን ማስከበር መስዋዕትነትን የሚጠይቅ ነው። የጣሊያንን ፋሺስት ወራሪ ጦር የታገለው ህዝባችን ቢያንስ አንድ ሚሊዮን ህይወትን ገብሯል። የአጼውን አገዛዝ ለመጣልም ሆነ የደርጉን አረመኔ ጭቆና ለማውደም ብዙ መቶ ሺ ዜጋ ተሰውቷል። በአሰቃቂው ሽብር ወርቅ ትውልድ ተመትሯል። የየካቲት 66 አብዮት የህዝብ አንድነትን ክንድ መፈርጠምና ውጤታማነት አሳይቷል - ድር ቢያብር አንበሳ ያስር እንዲሉ ነው። ዛሬ በፖለቲካው መድረክ የሚያተራምሱት ገንጣይ ኃይሎች የጋራ ትግል ባየለበት ወቅት ቦታም አልነበራቸውም። ዕድሜ ለወያኔ፣ የግንጠላና ክፍፍል መርዝ ተረጭቷልና በአሁኑ ጊዜ የገንጣዮች መንጋና አጫፋሪዎቻቸው እየተንጫጩ ናቸው። ዕብሪትም ይዟቸው አፋቸውን ሞልተው የአንድነት ኃይል ጭራሽ የለም የሚሉ ከሀዲዎችም በዝተዋል። ሀገራችንንም አመቻችቶ ለገንጣዮች አሳልፎ ለመስጠት ተገዝተውም ሆነ ተወናብደው የተሰማሩ ማፈሪያዎች አሉ። የመለስ አገዛዝ ውድቀት መቅረቡ ግልጽ ነውና ለውጡ ሕዝባዊ ሳይሆን በባዕዳን ቁጥጥር ሥር መሆኑን የሚደግፉ ክፍሎች ጥርሳቸውን ነክሰው እየተሯሯጡ ናቸው። ቅጥረኞቻቸውም እየቧረቁና እያጓሩ ናቸው። በመሆኑም የሀገር ማዳኑ ግዳጅ በጣም አሳሳቢና ወቅታዊም ሆኖ ይገኛል ።

በአንድነት ኃይሎች ላይ ጸያፍ ዘመቻ ተከፍቷል። ማጥላላቱና ማክቸልቸሉ በዝቷል። የባሰባቸው ቅጥረኞችማ የአንድነት ኃይል የሚባል የለም እያሉም ነው። የማይካደው ሐቅ የአንድነት ኃይሎች መዳከማቸውና መተባበር ላይም ድክመት ማሳየታቸው ነው። ይህ ግን የሉም በሚል ሀገሪቷን ለገንጣይ የሚያሰጥ ሊሆን አይችልም--ሀገር አጥፊና ባንዳ ካልተሆነ በቀር። የአንድነት ኃይሎችን አክቸልችሎ ገንጣዮችን እያዳነቁ ኢትዮጵያን ሊያጠፉ የተነሱትን ለመቋቋም ሆነ ሀገርን ለመታደግ የአንድነት ኃይሎች መተባበር አለባቸው። ሕብረትና ትብብር ስንልም በአንድ በኩል ከሆነና ከተሳካ የድርጅቶችን ህብረት የሚመለከት ሲሆን በሌላ መሠረታዊ ይዘቱ ደግሞ ህዝብን በአንድነት መፈክርና ዓላማ ዙሪያ ማደራጀትና ማታገልን የሚመለከት ነው። ዋናውና ወሳኙ የአንድነት ኃይል የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው። ይህ ሀገሩን የሚወድ ሕዝብ በዘረኛው አገዛዝ ላይ፤ በባዕድ ወራሪዎች፣ መሬት ነጣቂዎችና ገንጣዮች ላይ በህብረት እንዲነሳ ማደራጀትና ማታገል ያስፈልጋል። በዚህም መሠረት ኢሕአፓ ለሀገር ወዳድ ዜጎችና አንድነት ኃይሎች ሁሉ የሚያቀርበው ጥሪ

- የኢትዮጵያን አንድነት በማስጠበቅ ይህን  የሚጻረሩትን ሁሉ ለመታገል በመነሳት፤
- በሀገር አንድነት ላይ ቅንጣትም ባለመደራደር፤
- የግንጠላ አቀንቃኞችና አጫፋሪዎቻችውን በማጋለጥና በመታገል፤

- ለሀገር አንድነትና ለዴሞክራሲ ከቆሙ ኃይሎች ጋር በማበር፤
- የሀገር አንድነት መሠረት የሆነውን ሕዝብ በማደራጀትና በማታገል፤

መፍትሔ እንፈልግ የሚል ነው።

እንተባበር። በጋራ ጸረ አንድነት ኃይሎችን እንታገል ። ኢሕአፓ ለዚህ ዓይነቱ ተግባራዊና ፍሬያማ ትብብር ዝግጁ ነውና በመልዕክቱ የሚስማሙ አለን እንዲሉት ይጠብቃል። ሕዝብን ለሀገር አድን ትግል ለማደራጀትም ጥረቱን ይቀጥላል። የግንጠላ ኃይሎችና አሳፋሪ አጃቢዎቻቸው መድረክ ያጣበቡት የአንድነት ኃይሎች ዝምታ ስለሰፈነ ነው። ጸረ አንድነቶችን ሁሉ ወግዱ እንበላቸው።

ኢሕአፓ ለአንድነት ኃይሎች

እንተባበር፤ በጋራ ሀገርን ለማዳን እንነሳ፤ የገንጣዮችንና ባዕዳንን ሴራ እናክሽፍ!

የሚል ጥሪን ያስተላልፋል።

ሀገርን ማዳን የሀገር ወዳድ ዜጋ ሁሉ ሀላፊነት ነውና ሕዝብም ሀገሩን ለማዳን አብሮ እንዲነሳ ኢሕአፓ ጥሪ ያደርጋል።



EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel . 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France